# የዓድዋ ድልና የየካቲት 12 የሰማዕታት ቀን መታሰቢያ ልዩ እትም







## የኢትዮጵያ የጦርነትና የጀግንነት ታሪክ ከዘመነ አሪት ጀምሮ እስከ ዛሬ።

ኢትዮጵያ የብዙ ታላላቅ ታሪኮች ባለቤት ነች። አያት ቅድመ አያቶቻችን በኦሪት ዘመን ከአይሁዶችና ከግብጻውያን ጋር ብዙ ተጋድሎ አድርገዋል፤ በመቀጠልም ቀይ ባሕርን በመርከብ አቋርጠው በመሻገር ከአረቦች ጋር ተፋልመው አያሌ ድሎችን ተጎናጽፈዋል፤ እንዲሁም ከክርስቶስ ልደት በኋላ በዘመነ ሰልጣኔ መግቢያ ወቅት ከቱርኮች፤ ከግብጾች፤ ከጣሊያኖች፤ ከእንግሊዞችና ከማሃዲስት ሱዳናውያን ፤ ጋር አያሌ እልህ አስጨራሽ ታላላቅ ጦርነቶችን አካሂደው ድል አድረገዋል። አባቶቻችን ልጆቻቸውን ጀሮአቸንው እየቆነጠጡ የቀደሙ ታሪኮችን ያስምሩዋቸው ነበር፤ ጠንካራና ጀግና እንዲሆኑላቸው አደን፤ ጉግስ፤ ኢላማ፤ ጦር ውርወራ፤ ባህላዊ እስፖርት፤ ነጻ ትግል፤ ያለማምዱቸው ነበር። ያትውልድ በዘር፤ በሃይማኖት፤ በቋንቋ የተከፋፈለ አልነበረም፤ ጠላቱና ወዳጁን ለይቶ የሚያውቅ ትውልድ ነበር፤ ድሮ ወኔ የሚሰልቡ፤ ማንነት የሚያኮላሹ፤ ነገሮች ተለይተው ይታወቁ ነበር። ድሮ መረን በለቀቁ ሱሶች መጠመድ ነውር ነበር። ድሮ መቀራረብ፤ መመካከር፤ መነጋገር፤ መከባበር፤ መደማመጥ፤ ተከራክሮ ውሳኔ ላይ መድረስ የተለመደ ነበር። አገር ሉዓላዊ፤ ሁሉም ህዝቦች ኢትዮጵያዊ ነበሩ። አንድነትና፤ ባንዲራ ትልቅ ምስጢር ነበሩ። በዚህ ምክንያት ነበር ኢትዮጵያውያን በአለም የተፈሩና የተከበሩ ሆነው ከራሳቸው አልፈው ለተበደሉ ሕዝቦብ መቆም የቻሉት። በአባቶቻችን የተደረጉ ተጋድሎዎች በብዙ ታላላቅ ክፍሎች ለይቶ መመልከት ይቻላል። በአንደኛ ደረጃ ኢትይጵያን በነጻነት ለማቆየት ያደተደርጉት ተጋድሎዎች ሲሆኑ፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በሌሎች አገሮች የተወረሩና የተበደሉ አገሮችን ከጥቃት ለማዳንና ነጻ ለማውጣትነበር፤ ሶስተኛ አገራአችን ኢትዮጵያ በዓለም የኀይል ሚዛን ውስጥ እጅግ ወሳኝነት ያለው ጂአግራፊያዊ አቀማመጥ ባለቤት በመሆኑ፤ አራተኛ የታላቁ የአባይ ወንዝ የባለቤትነት ጥያቄ፤ አምስተኛ ሀይማኖትን የማስፋፋት አባዜ መከላከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው ለማለት ያስደፍራል። እነዚህ ከኦሪት እስከዛሬ ሳያቋርጡ አብረውን የኖሩ ችግሮች የኢትዮጵያ የጦርነት ታሪክ ምክንያት ሆነው እናገኛቸዋለን። በዚህ መሰረት አባቶቻችን በተሰዉላቸው የአድዋና የሌሎች በርካታ ድሎች ምክንያት ከሌሎች የአፍሪካና በአለም ዙርያ በጣት ከሚቆጠሩ ጥቂት አገሮች ተለይተን በነጻነት እንድንቆይ ረድቶናል።

በመሆኑም አንዳንዶች የታሪክ ድሆች እንደሚያስወሩት የኢትዮጵያ የድልና የስልጣኔ ታሪክ የ3 ሺ ወይንም የመቶ አመታት ብቻ አይደለም ። እግዚአብሄር ሰማይና ምድር ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ዘፍጥረት ም. 2 ቁ 8-16 ፤ ዘኀገሥት ም.1 ቁ 11፤ ዜና መዋዕል ም.9 ቁ 10 እንዲሁም በሳይንሱ ዓለም የድንቅነሽ (ሉሲ) ታሪክ ያጤኗል ። ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱ አያሌ ታሪኮች እስከዛሬ ድረስ ተከብረው እንዲቆዩ ደማቸውን አፍሰው አጥንታቸውን ከስከሰው ውድ ሕይወታቸውን ሰውተው የብዙ ቅርስ ባለቤት እድንሆንና አገራችንንና ህዝባችንን በነጻነት ጠብቀው ያስረከቡን አባቶቻችን ልንወዳቸው፤ ልንዘከራቸውና አርአያነታቸውም ልንከተል ይገባል።

የኢትዮጵያ ታሪክ ተነግሮ፣ ተጽፎና ተዝቆ የሚያልቅ ባይሆንም፣ ከአኩሪ ገድሎቻችን ውስጥ ጥቂቶቹን ለማስታወስ ያህል ከመጀመሪያው የሰው ልጆች ታሪክ ከሆነው መጽሀፍ ቅዱስ፣ ከተለያዩ ፈላጽፎችና ከታሪክ ተመራማሪዎች የተነገሩትን ጥቂት ምሳሌዎች እንመልከት።

*መጽሃፍ ቅዱስ ዘፀአት 3:21-22..... (የግብጽና ኢትዮጵያ ግጭት ጥንታዊነት)*
*ነቢዩ እግዚአብሄር ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ነጻ ለማውጣት ከመነሳቱ በፊት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ኢትዮጵያዊቷን ሲፓራን አግብቶ ልጆች ወልዶ የኖረው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው የአመራር ስልጠናውም ያገኘው ከኢትዮጵያዊው አማቱ ከካህኑ ከዮቶር ነው፣.... (ምንጭ ዶክተር ለይኩን ብርሃኑ በሃይማኖት ካባ ምጽሀፍ ገጽ 14-15)..... ሙሴ ወደ ኢትዮጵያ የመጣውም የኢትዮጵያና ግብጽ ውዝግብ ከአረት ዘመን ጀምሮ የነበረና ዛሬም ያለ ነው፤ በመጀመሪያ ግብጽ የአባይ ውሀ ለመተቀም እንድትችል በየዘመኑ ለኢትዮጵያ ገንዘብ ወርቅና የማዕድን ውጤቶችን ትሰጥ ነበር ስታቋርጥ ደግሞ ኢትዮጵያ ውሃውን እገድባለሁ እያለች ታስፈራራ እንደነበረ ታሪክ ይናገራል በመጨርሻ ጠባቸው እየከረረ በመጣ ጊዜ ሙሴ 400 ፈረሰኛ ሰራዊት ይዞ ኢትዮጵያ ከደረሰ በኋላ ነቢይና የእግዚአብሄር መላዕክተኛ በመሆኑ ጉዳዩ በሰላም እንዲፈታ አድርጎ ግብጽ የሚገባትን ከፍያ እንድትቀጥል ኢትዮጵያም ውሃ እናዳትከለክል በሰላም መጨረሱና ለተወሰኑ ጊዜያት አገራችን ውስጥ ቆይቶና ኢትዮጵያዊቷ ሲፓራን አግብቶና ልጆች ወልዶ ወደ ግብጽ መመለሱን እንረዳለን።*

*መጽሀፍ ቅዱስ ዜና መዋዕል መዕራፍ 14 ቁ 9-14.........( ከአሪቱ የጦርነት ታሪካችን)*
*ንጉሥ አቢያ ሞተ በዳዊት ከተማ በሚገኘውም በነገስታት መካነ መቃብር ተቀበረ በእርሱም እግር ልጁ አሳ ነገሰ..... (9) ዜራሕ ተብሎ የሚጠራ ኢትዮጵያዊ አንድ ሚሊዮን ወታደሮችና ሶስት መቶ ሠረገላዎች ይዞ ይሁዳን ለመውረር እስከ ማሬሻ ገስግሶ ደረሰ (10) አሳም ጦርነት ሊገጥመው መጣ ሁለቱም ወገኖች ማሬሻ አጠገብ በሚገኘው ጼፅፋታ ሸለቆ በታ በታቸውን በመያዝ ለውጊያ ተዘጋጁ (11) በዚህ ጊዜ አሳ ወደ አምላኩ እግዚአብሄር ጸለየ.......(12)ከዚህ በኋላ አሳና የይሁዳ ሰራዊት በኢትዮጵያ ሰራዊት ላይ አደጋ ጣሉ እግዚአብሄርም የኢትዮጵያ ሰራዊትን ድል አደረገ ኢትዮጵያውያንም ሸሹ (13) አሳና ሰራዊቱም እስከ ገራር ድረስ አሳደዱዋቸው ከኢትዮጵያ ሰራዊት ብዙ ሰዎች አለቁ ሰራዊቱ እንደገና ተንሰራርቶ ሊዋጋ አልቻለም በዚህ አይነት ሁኔታ ኢትዮጵያውያን በእግዚአብሄርና በሰራዊቱ ድል ሆኑ የንጉስ አሳ ሰራዊትም እጅግ የበዛ ምርኮ ወሰዱ (14) በዚያ አካባቢ የነበሩ ሕዝቦች እግዚአብሄር ባደረገው ነገር እጅግ ተሸብረው ነበር...።*

*ትንቢተ ኤርሚያስ ኢሳይያስ ም 18ቁ (1-17) .....(እግዚአብሄር ከትዮጵያ ጋር ስመሆኑ)*
*እናንት ፈጣን የሆናችሁ መላክተኞች ሂዱ ቁመታቸው የረዘመና ቆዳቸው ለስለስ ያለና ድል አድራጊዎች ወደሆኑ በአለም ሁሉ የመፈራት ግርማ ወዳላቸው በወንዞች የተከፋፈለ ምድር ወዳላቸው ህዝብ (ኢትዮጵያ) ገስግሳችሁ ድረሱ የሰራዊት ጌታ ከነዚያ ሕዝብ መባ የሚቀበልበት ጊዜ ይመጣል፤ እርሱም የሰራዊት ጌታ ወደሚመለክበት ወደጽዮን ክርብታ ይመጣሉ።*

*ደራሲ መስፍን ኃይሉ አደራ በተሰኘው መጽሃፋቸው ገጽ 18 .....*
*ሀ/ ማኒ የተባለ የተባለ ጥንታዊ የፋርስ ጸሐፊ ሂስቶሪካ አውጉስታ በተባለ መጽሃፉ (ከ216-276) የአክሱም መንግስት በወታደርና በጦር መሳሪያ የበለጸገ እንደሆነና ለወዳጅ አገሮቹ እርዳታ በመስጠት የታወቀ ነው፤ ብሏል።*
*ለ/በ1292 የባሕር ላይ ጉዞውን የጀመረው ማርኮፖሎ የጻፈውን መሰረት በማድረግ ። "ሊታወቁት የሚገባ ነገር አለ።..በአበሻ ምድር ምርጥ የሆኑ ወታደሮች አሉ። አብዛኛዎቹ ፈረሰኞች ናቸው። ፈረሶች በብዛት አሏቸው። በዚህም ምክንያት ተዋጊዎችና ሀይለኞች ናቸው። « ከምናደንቃቸው እውቅ የሕንድ ወታደሮችም የሚበልጡ ናቸው በማለት ጽፏል»*

## የኢትዮጵያ የጦርነትና የድል ታሪክ በአክሱም ዘመን ምንግሥት

*** " በአራተኛው መዕተ አመት በአክሱም ነግሶ የነበረው ኢዛና ግዛቱን በማሥፋፋት በጀግንነት የተዋጋቸውና በጦርነት ያስገበራቸውን የሚገልጹ በግሪክና በግዕዝ ቋንቋ በድንጋይ ላይ የተጻፉ ማስረጃዎች አሁንም ይገኛሉ። እነዚህ ጽሁፎች የሚገልጹት የጀግንነት ተግባሩና ጦርነት ያደረገባቸው አካባቢዎችን ነው።

ይኸውም በቤጃ ሕዝብ፤ በጸራኒ፤ በኖባና በኑብያ፤ ካሱ በሚባሉ ሕዝቦች ላይ ጦርነት ተደርጎ እያሸነፈ እንዳስገበራቸው አንዳንዶችም ደግሞ እንደደመሰሳቸው ይገልጻል። ማስረጃውው የሚለው ኢዛና የአክሱም፤ የሂሚያር፤ የካሹ (ኩሽ) የሳባ፤የሐበሳት፤ የራይደን፤ የሳልሄን፤ የጽያም፤የበጋ፤ (የበጅያ) ንጉሠነገሥት በጠላት የማይሸነፈው የመሕርም ልጅ፤ የበጋ (የበጃያ) ሕዝብ በሸፈተ ጊዜ እንዲወጓቸው ወንድሞቻችን ሳይዛናንና ሐዴፋን ላከናቸው። እነሱም ወደ በጅያ አገር በደረሱ ጊዜ 6 ነገስታት ከነነገዳቸው ተገዝተው ገቡላቸው። ከዚህ በኋላ 6ቱን ነገስታት ከነልጆቻቸው፤ ከነሚስቶቻቸው፤ ከነነገዳቸው፤ ከነከብቶቻቸው ማረኳቸው።....አገራቸው ከለቀቁበት ጊዜ ጀምሮ በየቀኑ እስኪጠግቡ ድረስ ህብስት ጠላም ከስጋ ጋር እየተመገቡ አራት ወር ተጉዘው እኛ ዘንድ አክሱም ደረሱ። ቀጥሎም 4400 ህዝባቸውን አልብሰን ለነገስታቱን ሽልማት (ስጦታ) ሰጥተን በክብር አድርገን ደወለ ባይራን በሚባል አገር እንዲቀመጡ አደረግናቸው” ይላል === (ምንጭ ደራሲ መስፍን ሐይሉ አደራ ምጽሀፍ ገጽ 30-31)

*** ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት (ዘ ኢትዮጵያን ሮያል ክሮኒክል / 1967 በሚለው መጽሀፋቸው እንደጠቀሱት የንጉሥ ኢዛናን ጀግንነት እንዲህ በሚል ገልጸውታል። The last inscription gives an account of an expedition against the Noba of Nubia, now part of Sudan, as well as the inhabitants of Kasu who also lived in the..... By the might of the lord of all I made war upon noba for the people of Noba had rebelled and made a... of it.... And I followed the fugitives for twenty three days, killing and making prisoners... Meanwhile I their towns those buile of brick and reads and..... I to Kasu and I fought a battle and made prisoners of its people at the junction of the rivers Siole (Nile) and Tekeze.

(ትርጉም)... “የኖባ ሕዝብ በማመጻቸውና ጉራ በመንዛታቸው በእግዚአብሄር ኃይል በነሱ ላይ ጦርነት አደረግሁ። ለማምለጥ በመሸሽ ላይ የነበሩ ለ23 ቀናት ተከታትዬ ገደልኳቸው። እሥረኛም አደረግኳቸው። ከጭቃና ድንጋይ የተገነቡ ከተሞቻቸውን አቃጠልኩ። ወደካሱ ሕዝብ መጥቼ የአባይና የተከዜ ወንዞች መገናኛ ቦታ ላይ ጦርነት አካሂጄ ሕዝቦቻቸውን እስረኛ አደረኳቸው” ይላል።

በአክሱም መንግሥት ከኢዛና በኋላ በአጼ ካሌብ ጊዜ ሌላ ትንሣኤ አግኝቶ ገናና እንደነበረ እንረዳለን። ከአጼ ካሌብ የጦር አለቆች አንዱ አብርሃም የተባለው የጦር መሪ በውጊያ አሸንፎ የየመን ከተማ በሆነችው በሰነዓ ብዙ ሕንጻዎችን ማሰራቱን። በወረራ እዚያ የነበረው የአይሁድ ንጉሥም በማስወገድ ወደካሌብ ግዛት በመጨመርና ቀይ ባህርን በመቆጣጠር የመን የአክሱም መንግሥት አካል ሆና እንደቆየች፤ እንዲሁም አብርሀም በ570 ዓ.ም መሳሪያ በጫኑ ዝሆኖች እየታገዘ መካ ድረስ መዝመቱንና ነገር ግን ከጦርነት ይልቅ ሥጦታ ተቀብሎና ስምምነት ፈጥሮ ቅድስት ቦታውንም ከጥፋት ታግሶ መመለሱን ታሪክ ያረጋግጣል። ===(ምንጭ አደራ በመሥፍን ኃይሉ ገጽ 34)

*** ደራሲ ሠለሞን ዮሐንስ የኢትዮጵያ ወርቃማ ዘመናት በተሰኘው መጽሀፉ ገጽ 29- 31 ዲዮዶር የተባለ የሮማ ታሪክ ጸሀፊ ጠቅሶ እንደዘገበው ግብጽን በሙሉ የገዙ የመጨረሻዎቹ ነገስታት ኢትዮጵያውያን እንደነበሩና ኢትዮጵያ ግን በማንም ተገዝታ እንደማታውቅ አብራርቶ ገልጿል።

እንደዚሁም ከላይ በተመለከተው መጽሀፍ ገጽ 34 ማኒ የተባለው የፋርስ ምሁር ዋቢ በማደረግ እንደተዘገበው ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአክሱም መንግስት በጊዜው ከነበሩት 4 ሀያላን መንግሥታት ከፋርስ፤ ከሮምና ከቻይና ተመጣጣኝ የሆነ ሀይል የነበረው አራተኛ አገር ነበረ ብሏል። በዚሁ መሰረት በጎረቤት አገሮች ችግር ሲፈጠር አቤቱታ ለአክሱም መንግሥት ይቀርብም እንደነበረ ተጠቅሷል።

*ልዩ ልዩ የአውሮፓውያን ኢትዮጵያን የመውረር እቅድና የዜጎች ተጋድሎ*

በአፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግስት በ1517 ዓም ከግራኝ ሙሃመድ ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ኢትይጵያን ለመርዳት ከፖርቱጋል በዶም ክርስቶፎር እየተመሩ የመጡት 400 ወታደሮች አካል የነበረው አባ ቤርሙዴዝ የተባለ ኢጣሊያናዊ ለአጼ ገላውዴኦስ "ከአባትዎ ከአፄ ገላውዴዎስ ጋር በተነጋገርነው መሰረት የኢትዮጵያ ግማሽ መንገስትና የቤተክርስቲያን አስተዳደር አስረክቡን" ብሎ ጥያቄ ማቅረቡንና አጼ ገላውዴዎስም ንግግሩን በጥሞና አድምጠው በሰጡት መልስ " እኔ እንዲህ አይነት ውለታ እንደነበራችሁ አባቴ አልነገሩኝም ስላደረጋችሁልን እርዳታ እናመሰግናለን ኢትዮጵያን የወደደ ይቆይ አልፈልግም ያለ የድካሙን ዋጋ እየተቀበለ ወዳገሩ ይሂድ፤ ከዚህ በተረፈ በአገሬ ላይ አንዳችም የውጭ ባንዲራ እንዳይሰቀል" ማለታቸውን ተከትሎ በተነሳው ውዝግብ ነገሩን ያነሳው አባ ቤርሙዴዝ ከፋ ተልኮ መታሰሩንና ከዚያ በኋላ በብዙ አማላጅና ጥረት ተፈቶ ወደ ሮማ ከተመለሰ በኋላ ልዩ ቡድን አቋቁመው ከኢትዮጵያ ምሁራንን አስኮብልሎ ወደ ሮማና ቫቲካን በመውሰድ ለወረራ የሚረዳቸውን የኢትይዮጵያ ልዩ ልዩ ባሕል፤ ቋንቋ፤ ታሪክ፤ ግዕዝና ሃይማኖት ሳይቀር ጥናት ሲያካሂዱ መቆየታቸው ከታሪክ እንረዳለርን። ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ተመልምለው የተወሰዱና እስከመጨረሻ እዚያው ቀርተው ሞተው የተቀበሩ ዜጎች ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው።

** 1ኛ አቦ ተስፋ ጽዮን ከሰሜን 2ኛ/ አባ ማርቆስ ከዳውሮ 3ኛ/ አባ መቃርዮስና 4ኛ/ አባ ጊዮርጊስ ከደብረ ሊባኖስ 5ኛ/ አባ ሀብተማርያም ከበጌምድር 6ኛ/ አባ ተክለሃይማኖት ከዲማ 7ኛ/ አባ እንጦኒዮስ ከጣቁሳ 8ኛ/ አባ ያዕቆብ ወ.ዘ.ተ ሲሆኑ ጊዜውም በ1559 ዓ.ም ነው፤ ስለሆነም በስበብ አስባቡ የተለያዩ ምክንያቶች እየፈጠሩ ወዳገራችን በመግባት እጅግ ብዙ የሰለላ ስራዎችን ሲያካሂዱ፤ ዜጎችን እያስኮበለሉ ምስጢር ሲሰበስቡና መንገድ ሲያጠኑ ኖረዋል። ...(ምንጭ ደራሲ አቶ አስረስ የኔ ሰው የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሀፍ ገጽ 3)

## አፄ ምኒልክ የአድዋ ጦርነት መንስኤ የሆነውን የውጫሌ ውል ለምን ፈረሙ?

በኢትዮጵያ የጎንደር ማእከላዊ መንግስት መጨረሻዎቹ ዘመናት እንግሊዞችና ጣሊያኖች እየተባበሩ የኢጥዮጵያ መኳንንትና መሳፍንትን በመሳሪያ እየገዙ በማታለልና እርስ በእርሳቸው እያዋጉ ዘመነ መሳፍንት እንዲፈጠር አደረጉ። በዚህ ሂደትመኳንንቱና መሳፍንቱ እርስ በእርሳቸው እየተጣሉም ቢሆን የውጭ ወራሪ በሚመጣ ጊዜ በጋራ ቆመው በመከላከላአቸው የውጭ ሀይሎች ሃሳባቸው ተሳክቶ አገሪቷን መቆጣጠር አልቻሉም። ነገር ግን ማዕከላዊ መንግሥትን በጣም ለማዳከምና ሕዝቡንም መከፋፈል ችለው ነበር።

በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ነበር አፄ ቴዎድሮስ ድንገት ብቅ ብለው ኢትዮጵያን መታደግ የቻሉት። መኳንንቱ፤ ማሳፍንቱና የቤተክርስቲያን ሰዎች ግን በንጉሡ ነገሥቱ ላይ ልዩ ልዩ አመጽ በማስነሳታቸው፤ በመጨረሻም ከእንግሊዞች ጋር በተደረገው የመቅደላ ጦርነት ላይ የአጼ ቴዎድሮስ ህይወት አበቃ። ከዚያ በኋላ አፄ ዮሓንስ ቢተኩም የቱርኮች፤ ግብጾችና ማአሃድስቶች (ሱዳን) በኢትዮጵያ ላይ ያደረጉት ዘመቻ በተለይም ጣሊያን፤ እንግሊዝና አረቦች ኢትዮጵያን አዳክሞ ለመያዝ ያደረጉት ያላቋረጠ ትግል ባስገኘላቸው ውጤት የአገራችን መከላከያ አቅም ተዳክሞ ጣሊያኖች ኤርትራን ሊይዙ ቻሉ።

በተጨማርም ኤርትራ በጣልያኖች ቅኝ ግዛት ስር የወደቀችው የኢትዮጵያ መኳንንቶች በማእከላዊ መንግሥት ላይ እየሸፈቱ ለውጭ መንገሥት በመርዳታቸው መሆኑን ከነዚህም ውስጥ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ሰለሞን የአካለ ጉዛይ ገገር፤ ደጃዝማች ደብብ አራአያና ባላምባራስ ክፍለየሱስ የከረን ገርዎች ወ.ዘ.ተ. መሆናቸውን ታውቋል።==

ምንጭ (አጤ ምኒልክ በጳወሎስ ኞኞ ገጽ 138 )

አፄ ምኒልክ ኢትዮጵያ ዙርያዋን በጠላት መከበብዋን በመረዳታቸው በሁለቱ አገሮች መካከል መልካም ግንኙነት መፍጠር መስሎአቸው ግንቦት 13 ቀን 21 1883 ዓም የውጫሌ ውል ሊፈርሙ በቁ ።



ይህ የውጫሌ ውል ካውንት አንቶሎኒ በሚባል ጣሊያናዊ አማካይነት በሁለት ቋንቋ በአማርኛና በጣሊያንኛ ተጽፎ ከተፈረመ በኋላ አንቀጽ 17 ሲተርጎም ተንኮል ያለበትና ሁለት ትርጉሞች ያሉት ሆኖ ተገኘ ። አፄው በኢጣልያንኛ የተጻፈው ስህተት ያለበት ስለሆን ታርሞ እንዲስተካከል ለአቻቸው ለጣልያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶ ደብዳቤ ልከው ቢጠይቁ የማይቻል መሆኑን በመግለጽ ይባስ ብሎ ጣሊያን ይህንን ውል መሰረት በማድረግ ለ12 የአውሮፓ መንግሥታትና ለአሜሪካ ደበዳቤ በመጻፍ ማንኛወም የኢትዮጵያ ጉዳይ የሚፈጸመው በጣሊያን አማካይነት መሆኑን አስታወቀ።, በማከታተልም  የአውሮፓ መንግስታት የባሪያ ሥርአት ለማስቀረት አውሮፓ ላይ ባደረጉት ስብሰባ ላይ ተወካያቸው የውጫሌ ውል የጣሊያንኛውን ትርጉም ይዞ በማቅረብ ኢትዮጵያ በጣሊያን ሥር ሆናለች በማለት ሪፖርቱን ለጉባኤው አቀረበ።

ለአድዋ ጦርነት ዋና መንስኤ የሆነው የውጫሌ ውል አንቀጽ 17 ትርጉሙ እንደሚከተለው ነበር።.
ሀ/ የአማርኛው ትርጉም....ኢትዮጵያ ከውጭ መንግሥታት የምትፈልገው ጉዳይ በጣሊያን መንግስት አጋዥነት መላላክ ይቻላታል የሚል ሲሆን፤
ለ/ የጣሊያንኛው ትርጉም ግን.... ኢትዮጵያ ከውጪ መንግስታት ጋር የምታደርገው ግንኙነት በጣሊያን መንግሥት አማካይነት ማደረግ ይገባታል የሚል ነበር። የአማርኛው ትርጉም ኢትዮጵያን ለማገዝ እርዳታና ትብብር የሚያመለክት ሲሆን የጣሊያንኛው ትርጉም ግን ማድረግ ይገባዋል የሚለው ቃል ግዴታ የሚያስገባና የጣሊያንን መንግሥት የበላይ የኢትዮጵያን መንግሥት የበታች የሚያደርግ ነበር።

ይኸው ተንኮል የተመላበት የውጫሌ ውል መሠረት በማድረግ የጣሊያን መንግስት የዲፕሎማቲክ ዘመቻውን በማስፋፋት ለ12 የአውሮጳ መንግስታትና ለዩናይትድ እስቴትስ በተደጋጋሚ ደብዳቤ በመጻፍ ኢትዮጵያ በጣሊያን መንግስት ሥር መሆኑን አሳወቀ።



አፄ ምኒልክም በበኩላቸው የውጫሌ ውል አንቀጽ 17 የጣልያንኛ ትርጉም ተንኮል ያለበት መሆኑና ተቀባይነት እንደሌለው ለዓለም መንግስታት አሳወቁ። በዚሁ መሰረት የውጫሌ ውል በአፄ ምኒልክ ውሳኔ ከፈረሰ በኋላ የጣሊያኖች ምርጫ ጦርነት ሆኖ በኤርትራ በኩል ወደመሀል አገር እየገሰገሱ ብዙ ቦታ መያዝ ጀመሩ።

በ1887 በጄኔራል አሬሮ የሚመራ ጦር ከኤርትራ ወደ ትግራይ በማስገባት የራስ መንገሻን ጦር ወግቶ አጋሜን፤ እንደርታን፤ አምባለጌን አክሱምን አድዋን መውረሩ ተሰማ። በዚሁ መሠረት በጥር ወር 1887 ዓም ራስ መንገሻና ራስ አሉላ የጠላትን ጦር ኮአቲት ላይ ገጥመው ድል የመቱት ቢሆንም በጄኔራል ባሪያቴሪ መሪነት 17 ሺ አዲስ ጦር በማስመጣት ውጊያውን ቀጥሎ ጣሊያን አድዋንና አምባለጌን በመያዙ የኢትዮጵያ መንግስት በአፄ ምኒልክ አማካይነት የክተት አዋጅ አስነገረ ።

የአጼ ምኒልክ የክተት ጥሪ ፤ “አገር የሚያጠፋ ሃይማኖት የሚለወጥ ጠላት እግዚአብሄር የወሰነልኝን ባህር አልፎ መጥቷል ። አሁን ግን በግዚአብሄር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጥም ..ጉልበት ያልህ በጉልበትህ ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፤ ለሚስትህ፤ ለሃይማኖትህ ሰትል በጸሎትህ እርዳኝ “የሚል ነበር።

የጣሊያን ሹማምንትና ሕዝባቸው የኢትዮጵያን ህዝብን ድል በማደረጉ ተማምኖ በየቦታው በሚፈነጭበት ጊዜ በአዲስ አበባ ምኒልከጦራቸውን ሲያከማቹና ሲያደራጁ እቴጌ ጣይቱ ደግሞ በበኩላቸው በየአገሩ ያለውን ሸከላ ሠሪ

ሁሉ አሰባስበው የእንጀራ ምጣደና የወጥ መስሪያ ድስት ሲያሰሩከ ሰነበቱ በኋላ ሠራዊቱ ወደሰሜን ጦር ግንባር መትመሙን ቀጠለ ። መጣም የሚያስገርመው በዚህ ዘመቻ ላይ አዝማሪው፤ ለማኙና፤ ልጆች ሳይቀሩ መሳተፋቸውና ያበርከቱትም አስተዋጾ እጅግ ከፍ ያለ እንደነበረ ነው።

ከዚያ በኋላ በአፄ ምኒልክና በእቴጌ ጣይቱ የሚመራ ሠራዊት በመስከረም ወር 1888 ( አኦክቶበር 1895 ዓም) ከአዲስ አበባ ወደ ሰሜን ጦር ግንባር ለመዝመት እቅዱን ያጠናቅቀ ሲሆን ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነበር ።

1ኛ/አጼ ምኒልክ ከ 42 000 ሺህ ሠራዊት ጋር፤ 2ኛ/እቴጌ ጣይቱ ከ 9 ሺ ስራዊት ጋር፤ 3ኛ/ራስ መኮንን ከ15 ሺ ስራዊት ጋር፤ 4ኛ/ራስ ሚካኤል (አሊ) ከ11 ሺ ሰራዊት ጋር፤ 5ኛ/ ራስ መነገሻ ዮሃንስ ከ12ሺ ስራዊት ጋር፤ 6ኛ/ ራስ አሉላ ከ3ሺ ሰራዊት ጋር፤7ኛ/ ራስ መነገሻ አቲከም ከ6ሺ ሰራዊት ጋር፤ 8ኛ/ ራስ ወሌ ከ10 ሺሠራዊት ጋር፤ 9ኛ/ራስ ወልደጊዮርጊስ ከ8 ሺ ስራዊት ጋር፤ 10ኛ/ አዛዥ ወልደ ጻዲቅ ከ3ሺ ስራዊት ጋር ፤ 11ኛ/ ደጃዝማች ተሰማ ናደው ከ4ሺ ስራዊት ጋር፤ 12ኛ/ ራስ ዳርጌ፤ ግራዝማች በንቲ፤ ቀኛዝማች መኮንንና ፊታውራሪ ኃብተጊዮርጊስ ከ20 ሺ ስራዊት ጋር ወ.ዘ.ተ ።

ወደ አድዋ የዘመተው የኢትዮጵያ ሠራዊት ብዛቱ በትክክል አይታወቅም። ብዙ ታሪክ ፀኃፊዎች የዘገቡት የተለይየ ቁጥር ነው። ቶኪ የተባለ ጸሃፊ ከ70 ሺ እስከ 80ሺ ብሏል። አንቶሎኒ ደግሞ ከ110 ሺ እስከ 120ሺ ሲል የምኒልክ መድፍ አስተኳሽ የነበረው ፈረንሳያዊው ካፒቴን ክሎቼቴ 150ሺ እንሆናለን በማለት ጽፏል።====== == (ምንጭ አጤ ምኒልክ በጳውሎስ ኞኞ ገጽ 160)

በመጀመሪያ ጦርነቱ የተጀመረው አምባለጌ ላይ ነበር። ሕዳር 28 ቀን 1888 ዓም የኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ሠራዊት በሻለቃ ቶዞሊ የሚመራውን የጠላት ጦር አምባለጌ ላይ በራስ መኮንን፤ በራስ ወሌና በራስ መንገሻ ዮሃንስ ከሚመራው ሠራዊት ጋር ግንባር ለግንባር ተጋጠሙ። ይህ በእንዲህ እያለ በፊታውራ ገበየሁ ይመራ የነበረ 1200 ጦር በመድረስ ጠላትን ከቦ የቀዳሚ ጦር ውጊያ በመጀመር 6 ሰአት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የጣሊያንን ጦር ተደመሰሰ ። በዚህ ውጊያ 400 የጣሊያን ጦር ቁስለኛ ሲሆን 2000 የሚሆን ሠራዊት ወድሞ የተቀረውው የጣሊያን ሠራዊት ወደ መቀሌ ለማፈግፈግ ተገደደ ።

በአጭር ሰዓት ድል የሆነው ጣልያን እጅግ በመደናገጥ ሚጀር ሳልሳ ወደ ንጉሡ መላዕክተኛ በመላክ በጃችን ያለውን ይዞታ እውቅና ከተሰየን ነገሩን በስምምነት እንጨርስ በማለ ሃሳቡን ለአፄ መኒልክ አቀረበ ። አፄ ምኒልክና ካቢኔአቸው በጥልቀት ከተወያየበት በኋላ በተለይም እቴጌ ጣይቱና ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ አጥበቀው በመቃወማቸውና ንጉሡም ይኸው በመደገፋቸው ጣልያን ያቀረበው ሃሳብ ውድቅ ሆኖ አፄው የሚከተለውን መልስ ሰጡ ይኸውም "እኔ ይህንን መንገድ ሁሉ አቋርጬ ከሸዋ የመጣሁት የጣሊያንን ባንዲራ ለመቅደድ እንጂ አገሬ ላይ ለመስቀል አይደለም ።" በማለት የኢትዮጵያ መንግስት ምርጫ አሳወቁ ።
በመቀጠልም ኢትዮጵያውያኖቹ ወደ መቀሌ የሚሸሸውን ሠራዊት እየተከታተሉ በማሳደድ ይፈጁት ጀመር፤ በዚህ ጭንቅ ጊዜ ኢጣልያኖቹ አንዲት መንገድ ብቻ ክፍት ሆኖ በማግኘታቸው ቁስለኛውም ፈረሱም፤ በቅሎውም፤



ጤነኛውም በዚያው መንገድ እየተተራመሰና እየተጋፋ ሲሸሽ የኢትዮጵያ ጦር ማነጣጠር የማያስፈልገው ሆነ ። ሞልቴዶ የተባለ ጣልያናዊ እንደጻፈው "ራስ አሉላ እንዳያመልጥህ እያሉ በማዘዛቸው ከጣሊያን ወገን ብዙ ሰውና እንስሣት ተደመሰሱ ብሏል "በርክሌይ ደግሞ " ከአምባለጌ እስከ መቀሌ ርቀቱ 35 ማይል ነው፤ የሚሸሸው የጣልያን ሠራዊት መሄጃ መንገድ እያጣ መቀሌ የደረሰው ከሳምንት በኋላ ነው "ብሏል ።

በዚህ በአምባለጌ  ጦርነት 1300 የኢጣልያ ጥቁር ጦር፣ 20 ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ተገድለው የተቀሩትም በሰይፍ ራሳቸው ተገምሶና እጃቸው ተቆርጦ መቀሌ በመሰብሰብ የአምባለጌ ጦርነት በጣልያውያኖች አሰቃቂ እልቂት ተጠናቀቀ ።

ከየቦጦር ግንባሩ የሸሸው የጣሊያን ሠራዊት መቀሌ ላይ ተሰባሰበ ። ጣሊያኖች የመቀሌ ምሽግ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ጥንቃቄ ና ሊሰበር የማይችል ጉድባ አደራጅተው ከሰሩ በኋላ ምሽጉ ውስጥ ገብተው መኖር ጀምረው ነበር ። ኢትዮጵያውያንም በተለያዩ ጊዜያት ምሽጉን ሰበረው ለመገባት በዙ ሙከራ ቢያደርጉም በሰው ሃይል ወይም በመሳርያ ብዛት የሚፈታ አልሆነም።

ኢትዮጵያውያን ያንን አስቸጋሪ ምሽግ ሰብረው ለመግባት በሞከሩ ቁጥር ያስከተለውን እልቂት የተገነዘቡት እቴጌ ጣይቱ አንድ ምሽት ላይ በራሳቸው እዝ ስር ያሉትን ፀሃፊ ትዕዛዝ ሊቀመኳስ አባተና በጅር ወንድ ባልቻ አስጠሩና እንዲህ በማለት ተናገሩ “እንገዲህ ከዚህ ጉድባ ውስጥ ያሉትን ኢጣልያኖች ሳላወጣ ወዲያና ወዲህ አልልም እናንተም አረር እንዳይመታችሁ መታኮሻችሁን አብጁ” ብለው አዘዙዋቸው ።

በማከታተልም ንግሥቲቱ ምሽቱን ወደ ውጭ ብቅ በማለት የድንኳናቸው ግምጃ አስገልጠው ወደ ጣልያኖች ምሽግ እየተመለከቱ ከቆዩና ምን ማድረግ እንደሚሻል ካሰላሰሉ በኋላ ኢጣለያኖች የሚጠቀሙበትን የምንጭ ውሃ መያዝ በጣልያኖች ላይ የሚያስከትለውን ውድቀት መረዳት በመቻላቸው በራሳቸው ስር ያሉትን ሁለት የጦር ሃላፊዮቻቸው ከሆኑት ከአዛዥ አማኑኤልና ከሊቀመኳስ አባተ ጋር ተነጋገረው ምሽቱን የምንጩን ውሃ በራሳቸው ወታደሮች በአስቸኳይ እንዲያዝ አደረጉ ።
ምንጩን ከበው የያዙት የንግሥቲቱ ወታደሮች ብዛት 900 ያህል ነበሩ። እቴጌ ጣይቱ እንዴት ውሃውን እንዳስያዙት በተለያዩ ደራስያን እንደተገለጸው እጅግ የሚያስደንቅ የጦር እስትራቴጂ እንደሆነና ያስገኘውም ውጤት ተወዳዳሪ ያልተገኘለት እንደነበረ ተዘግቧል። ይኸውም በዚያን ጊዜ ይቅርና አሁን ጥበብ በበዛበት ዘመን እንኳን የማይታሰብ ብልሃት እንደሆነ ነው።

በዕቴጌይቱ ዘዴ ጣሊያኖች የሚጠቀሙበት የመቀሌ ምንጭ በኢትዮጵያውያን ከተያዘ በኋላ በኢጣልያኖች ሠፈር ትልቅ የውሃ እጥረት ተከሰተ። በየቀኑ የሚጠጣ የውሃ ራሽን ችግሩን ሊፈታ ካለመቻሉም በላይ በምሽጉ ውስጥ ያለው ሰራዊታቸውና እንሰሳት በውሀ ጥምና በበሽታ በማለቁ ጥር 9 ቀን ሙሴ ፊልተር የሚባል አማላጅና ተደራዳሪ ልከው እርቅ ጠይቀው በኢትዮጵያም በኩል ተቀባይነት በማገኘቱ የጣልያኑ ንጉስሥ ኡምቤርቶ በጻፉት ደብዳቤ አማካይነት የመቀሌ ምሽግ ለኢትዮጵያውያን እንዲያስረክቡ ትዕዛዝ ደርሶ የኢትዮጵያ ሰራዊት ምሽጉን ሊረከብ ቻለ።

በዚሁ መሠረት በጅር ወንድ ባልቻ ተልከው ምሽጉ ውስጥ በመግባት የኢትዮጵያ ባንዲራ ከተከሉ በኋላ የጣሊያን ወገን ሰራዊት ከብቱም ሰዉም ውሃ እንዲጠጡና በሠልፍ ሆነው ተራ በተራ ከምሽግ እንዲወጡ ተደረገ።

ከመቀሌ ምሽግ 20 ከፍተኛ መኮንኖች 13 ዝቅተኛ መኮንኖች 150 ባለሌላ ማእረጎች 1000 ጥቁር ወታደሮች 200 ቁስለኞች ሲለቀቁ 27 000 ጠመንጃዎች ተማርከው የመቀሌ ከተማና የጣልያን ምርኮኞች በኢትዮጵያውያን ቁጥጥር ስር ሊሆኑ ቻሉ ።



1



2



3



4

*ምስል 1ኛ ደጃዝማች ባልቻ አባነብሶ 2/ ራስ አሉላ አባነጋ 3/ ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ 5/ ራስ መኮንን ናቸው፤*

የአድዋ ድል፤ ስለ አድዋ ጦርነት በአገርና በውጭ አገር ደራሲያን እጅግ ብዙ የተጻፈ ስለሆነ ዝርዝሩን ማወቅ የሚፈለግ ሰው የተለያዩ መጻህፍትን ማንበብ ይችላል። ለዚህ መጣጥፍ ፍጆታ ያህል ግን ከዚህ በታች ያለውን እንመልከት። ጣልያኖች ከመቀሌ ተሸንፈው ከወጡ በኋላ ሃይላቸውን እንደገና አደራጅተው በድጋሚ ለአፄ ምኒልክ ከአሁን በኋላ ጦርነት እንዳይቀጥል ከፈለጋችሁ ይህንን የእርቅ ሃሳብ ተቀበሉን በማለት ማጆር ሳልሳ ይዕ ላይ ከሰፈሩት ከአፄ ምኒልክ ዘንድ ደርሶ 1ኛ/ራስ ቢትወደድ መንገሻ 2ኛ/ራስ መኮንን 3ኛ/ ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ በተገኙበት ያቀረበው አዲስ የመደራደሪያ ሃሳብ ባጨሩ እንዲህ የሚል ነበር ።



‘‘በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት ውስጥ ያሉ ሹሞች ሁሉ የኢጣልያን የበላይነት እንዲያውቁ፤ የኢጣልያን ግዛት ከአሸንጌ ሃይቅ እስከ ተከዜ ወንዝ ድረስ እንዲሆን፤ ጠቅላላዋ ኢትዮጵያ ደሞ በጣልያን ጥገኝነት ሥር እንድትሆን የሚል ነበር። አፄ ምኒልክ በጸጥታ ካዳመጡ በኋላ “ ይሄ ለጆሮ የሚቀፍ ለልብ የማይስማማ ነገር ነው። እኔ የመጣሁት የጣልያን ባንዲራ ልቀድ ነው እንጂ እንዲህ አይነቱ እርቅ ልቀበል አይደለም በተረፈ አምላክን ጨምሬ በመጣችሁበት መንገድ አስተናግዳችኋለሁ ባገሬ ላይ የሮማ ባንዲራ አይሰቀልም” ብለው መልስ በመስጠት ዳግም ውድቅ በማደረግ በሁለቱም በኩል የጦርነቱን መሰናዶ ተጧጡፎ ፍጥጫ ሆነ። በዚህ ድርድር ላይ አንዳንድ መኳንንት ተለሳልሰው የታዩ ሲሆን እቴጌ ጣይቱና ፊታውራሪ ኃብተጊዮርጊስ ግን የጣሊያንን ተንኮል በመገንዘባቸው እጅግ ጠንካራ አቋም ይዘው እንደተከራከሩ በታሪክ ተዝግቧል።




በዚሁ መሰረት ዋናው ጦርነት እስኪጀመር በየቦታው በተናጠል ቁርቋሶ ሲደረግ ሰንበቶ የካቲት 23 ቀን 1888 ከሌሊቱ 11 ሰዓት በጣልያን ቀድሞ ተንኳሽነት ተጀመረ የጦሩም አሰላለፍ በጄኔራል አልቤርቶኒ፤ ጄኔራል ባራቲየሪ፤ጄኔራል ባልዳሴራ ፤ጄኔራል ዳቦር ሜዳ፤ ጄኔራል አሌሴና፤ማጆር ቶዞሊ፤ማጆር ጋሊያኖ እና ቲንቲ ማንፍሬዲኒ ።

በኢትዮጵያ በኩል ራስ መኮንን የሃረርጌን ጦር እየመሩ አድዋ ከተማላይ፤ ራስ ሚካኤል የወሎን ጦር እየመሩ ሰላዶ ተራራ ላይ፤ ንጉሥ ተክለሃይማኖት የጎጃምን ጦር እየመሩከጣልያኖች ምሽግ ፊት ለፊት፤ራስ መንገሻ ዮሓንስ የትግራይን ጦር እየመሩ አዲ አቡን ላይ፤አፄ ምኒልክ እና እቴጌ ጣይቱ ራስ ወሌና ዋግሹም ጓንጉል ከኋላ በደጀንነት፤ የአኦሮሞ ጦር 13 ኪሎሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውን የውሃ ምንጭ ከበው ያዙ።

## በዓድዋ ጦርነት የመጨርሻ የጣሊያን ጦር አሰላለፍ

በአልበርቶኒ የሚመራው ብርጌድ በውስጡ በሜጀር ዱሪቶ የሚመራው 1ኛው ባታሊዮን 950 ወታደሮች ፤ በሜጀር ኮሱ የሚመራው 6ኛው ባታሊዮን 850 ወታደሮች በሜጀር ቫሊ የሚመራው 7ኛው ባታሊዮን 950 ወታደሮች በሜጀር ጋሜራ የሚመራው 8ኛው ባታሊዮን 950 ወታደሮች፤ በሌተና ሳታሊ የሚመራው ባታሊዮን 376 ወታደሮች፤



በኢንሪ የሚመራው የተራራ መድፈኛ ጦር ከ4 መድፎች ጋር፣ በሻቢ የሚመራው ሁለተኛው መድፈኛ ክፍል ከ2 የተራራ መድፎች ጋር፣ በቢያንኪ የሚመራው 3ኛ መድፈኛ ክፍል ከ4 መድፎች ጋር፣ በማሶዮ የሚመራው 4ኛው የተራራ መድፈኛ ክፍል ከ4 መድፎች ጋር፣ የነበሩት ሲሆን በጠቅላላው በአልበቶኒ እዝ ውስጥ 4076 ወታደሮችና 14 መድፎች ነበሩ።

በአርሞንዴ የሚመራው ብርጌድ ደግሞ በ14ኛው ሬጅሜንት ውስጥ ዲ.እስቲፋኖ የሚመራው ባታሊዮን 423 ወታደሮች፣ ኮምፒአና የሚመራው 350 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን፣ ብሩስቲ የሚመራው 2ኛሬጅሜንት ውስጥ ቪይአንቺኒ የሚመራው 450 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን፣ ዲ.አሚቺስ የሚመራው 500 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን፣ ባውዶይን የሚመራው 550 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን፣ ፓቪሲ የሚመራው 220 ወታደሮች፣ ፍራንዚኒ የሚመራው 11ኛ የተራራ መድፈኛ ክፍል ከስድስት መድፎች ጋር፣ በጠቅላላውበዚህ ብርጌድ ውስጥ 2493 ወታደሮችና 12 መድፎች ነበሩ።==( ምንጭ አጤ ምኒልክ በጳውሎስ ኞኞ ገጽ 196)

በኤልና በሚመራው ብርጌድ ውስጥ ደግሞ የ4ኛው ሬጂሜንት፣ አዛዥ ሮሚሮ የሚያዘው ሞንቲኪ የሚመራው 7ኛው የእግረኛ ባታሊዮን ከ450 ሰዎች ጋር፣ ቪዳንቲ የሚያዘው 450 ሰዎች ያሉበት ባታሊዮን፣ ማንፍሬዲ የሚያዘው 480 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን፣ ናና የኢያዘው ሬጅሜንት ውስጥ ደግሞ አልቴኒ የተባለው ተራራ ወጭ ባታሊዮን ከ550 ዕታደሮች ጋር፣ ፌራሮ የሚያዘው 85ኛው ባታሊዮን ከ500 ወታደሮች ጋር፣ ቫንዲዮል የሚያዘው 500 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን፣ ጋሊያኖ የሚያዘው 1150 ወታደሮች ያሉበት ባታሊዮን፣ ድ.ሮሳ በሚያዘው ሬጅሜንት ውስጥ 1ኛው መድፈኛ ክፍል ከስድስት መድፎች ጋርና ከ70 ኢንጂነሮች ጋር ሆነው 4150 ወታደሮች ነበሩበት። በጠቅላላው ኢጣሊያ አድዋ ላይ ያሰለፈው ዘመናዊ ጦር 14 069 ነጭ ወታደሮችና በጠቅላላው በጦሩ 56 መድፎች ነበሩ። ከዚህም ሌላ 1400 የጭነት ከብት የሚነዱ ዘመናዊ መሳሪያ የታጠቁ ወታደሮች  እንደነበሩ አኪሌ ቢዞኒ ጽፏል። (ምንጭ አጤ ምኒልክ በጳውሎስ ኞኞ ገጽ 197)

** የጦሩ ጠቅላይ  አዛዥ ጄኔራል ባራቲየሪ ሰራዊቱ ሌሊቱን እንዲንቀሳቀስ አዘዘ በኢትዮጵያ በኩል እንዲሁ የጣሊያንኖች ዝግጅት እንደተሰማ ሌሊቱን ወታደሩ እየተዘጋጀ፣ አዝማሪው እየዘፈነ ዘማቹ እየሸለለና እየፎከረ አደረና ጠዋት ውጊያው ተጧጧፈ የራስ መንገሻ ጦር ሊነጋጋ ሲል ከጄኔራል አልቤርቶኒ ሠራዊት ጋር እንዳ ኪዳነምህረት ላይ ተጋጠመ ፤ከንጋቱ 12 ሰአት ላይ አልበርቶኒ ሌሎች ጄኔራሎች እንዲደርሱለት እርዳታ ጠየቀ ወዲያወኑ ጦሩ በሙሉ በኢትዮጵያውያኖች ስለተቋረጠ መረዳዳ ያለመቻሉን ሰማ ።

ለአንድ ሰአት ሩብ ጉዳይ ሲሆን የጄኔራል ዳቦር ሜዳ ብርጌድ አልበርቲኒን እንዲረዳ ታዘዘ ረጂው ጦር 800 ሜትር ያህል እንደተጓዘ በትዮጵያውያን ተያዘ፤2 ሰአት ተሩብ ሲሆን ጄኔራል ባራቲየሪ ፈረስ ላይ ተቀመጦ ጦሩን ለማበረታታት ራዮ ተራራ ሄዶ ቁስለኞችና የሸሹ ወታደሮች ሜዳውን ሞልተውት በማየቱ እጅግ ተደናገጠ ።

ኢጣልያኖች በመድፍ ፤በመትረየስና፣ በቦምብ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ያለማቋርጥ ሲያዘንቡ የሚዘንበው እረር ከምንም ባለ መቁጠር ኢትዮጵያውያኖች ሰንጥቀው እያለፉ ፈጁት። የከባድ መሳርያውንም ተኩስም ዝም አሰኙት በጥቂት ሰአቶች ውስጥ 81 መኮንኖች እና 48 ወታደሮች ሙት ሆኑ የተረፉት ተማረኩ የተቀሩት እግሬን አውጭኝ አሉ የባታልዮኑ መሪ ጋልያኖ ቆስሎ ተማረከ፣ ረፋዱ ላይ ጄኔራል ባራቲየሪ ተማረከ፣ ጄኔራል አርሞንዲ፣ ማጆር ቶዞሎኒ፣ ማንፍሬዲኒ ማጆር አንጊራ ሁሉም አለቁ ።    


1

2

3

4

5

ምስል 1/ጄኔራል ባራቲየሪ 2/ ጄኔራል አልበርቶኒ 3/ ጄኔራል ባልዴሴራ 4/ ጄኔራል ዳቦር ሜዳ 5/ ማጆር ጋሊያኖ

በዚህ እጅግ አስከፊና አሰቃቂ ጦርነት በስለላ ስራ ለኢትዮጵያ ወገን እጅግ ከፍተኛ ውጤት ያስገኘ የመረጃ አገልግሎት ያበረከቱት የሐማሴን ተወላጆች ባሻ አዋአሎምና አቶ ገብረእግዚአብኄር ነበሩ ።

ታሪኩን ለማሳጠር በአድዋ ጦርነት 7560 ኢጣልያኖችና 7100 ጥቁር ወታደሮች ሲገደሉ 954 ኢጣልያኖች ጠፍተዋል 470 ኢጣልያኖች 958 ጥቁር ወታደሮች በድመሩ 1428 የጠላት ወታደሮች ቆስለዋል፤ 11000 ጠመንጃና 56 መደፎች ሲማረኩ በትዮጵያ በኩል ደግሞ 70 ሺ ሞቱ 10ሺ ቆስለው ድሉ የኢትዮጵያ ሆኖ ተደመደመ ።

"እጅግ ብዙ ወታደሮች ያሉት የአውሮፓ ጦር በአፍሪካ ሰዎች ለመጀመርያ ጊዜ ተዋረዶ ተሸነፈ። በዘመናችን ታሪክ ውስጥ እንደ አድዋ ጦርነት ያለ የለም። የደረሰው ዕልቂትም ለመግለጽ የሚያስቸግር ነው፤ የጣልያን ጦር በአንድ ቀን ጀንበር ተጠናቀቀ። ፖለቲካና ታሪክ አበቃ። በአፍሪካ ውስጥ ታላቅ የተወላጆች ሃይል መነሳቱ ታወቀ የአፍሪካ ተወላጆች ታሪክ ተለወጠ ። ጥቁሩ ዓለም አውሮፓውያን ላይ ሲያምጽና ሲያሸንፍ ይህ የመጀመሪያ ነው። አበሾች አደገኛ ህዝቦች መሆናቸው ከአሪት ዘፍጥረት ጀምሮ ተጻፏል። የኛ ዓለም ገና ቶር እና አዲዮን በሚባሉ አማልክት በሚያመልክ ጊዜ አበሾች የክርስትና ሃይማኖት የተቀበሉ ናቸው። አሁን ሁሉም ነገር አድዋ ዘጋው "ከቤርክሌይ ማስታወሻ ጳውሎስ ኞኞ የጻፈው።

አጼ ምኒልክም ያገኙትን ድል በማስመለከት መጋቢት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ለሩስያው አቻቸው ለንጉሠ ነገሥት ዊሊያም ፤ለሮም ሊቀጳጳስ ሊዮን 13ኛ፤ ለስፓኙ ንጉሥ አልፎንዞ ፤ለፖርቱጋሉ ንጉሥ ለቀዳማዊ ቄርሎስ ፤ ለስዊስ ፕሬዚዳንት፤ ለቤልጂግ ንጉሥ ለዳግማዊ ሊዮፖርድ፤ ለፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ለሙሴ ፌልክስ ፎርናለሌሎችም ብዙ መንግስታት ደበዳቤ ጽፈው አስታወቁ ።

<u>የአድዋ ጦርነት በውጭ አገር ፀሐፍት</u>

"የተተከለው ድንኳን ሲታይ ከብዛቱ የተነሳ አፍሪካ ኤሮፓን ለመጠራረግ የተነሳች ይመስላል ። የጦርነቱ ዕለት ኢትዮጵያውያኑ ደማቅ ቀለም ያለው ካባ ለብሰው፤ ጠመንጃና ጦር ይዘው፤ጎራዴ ታጥቀው፤ የነብረና ያንበሳ ቆዳ ለብሰው ጸሀይዋ ፈንጠቅ ስትል በተራራው ላይ በታዩ ጊዜ የኢጣልያን ጦር አሸበሩት" ...በርክሌይ

"ውጊያው እስቲጀመር እንጠብቃለን ...እህቴ ሆይ ይህ ደብዳቤ ሲደርስሽ በህይወት እንደሌለሁ ቁጠሪው። በህይወት የምትቀሪው አንቺ እህቴ ለታዘዝኩት ሥራ በክብር መሞቴና በክብር መሞት ደግሞ ለሰው ልጅ አስፈላጊ መሆኑን መስክሪ" ....ካፒቴን ካኖቫቲ ለእህቱ ከጻፈው ደብዳቤ ላ.ጉየራ ኢን አፍሪካ ከሚለው መጽሀፍ የተወሰደ

“ በእንዲህ አይነቱ የጭንቅ ጊዜ መልካም ምኞቴን ልገልጽልህ እወዳለሁ።... ጥቂት ሰዓት ከሚያስኬድ ርቀት ላይ ራሶች ተሰልፈዋል ። በአንድነት ወደኛ ይጓዛሉ፤ ባታሊዮናችንም እንድናፈገፍግ ብቻ ይነግረናል። የዚህ ውጤት መጨረሻው ምን እንደሆን ይገባሃል፤ ጦሩ እየገፋ እስቲመጣ ድረስ ብቻ እንጠባበቃለን። ....ለታዘዝነው ትእዛዝ ሕይወታችንን እንሰዋለን፤ የኛ ነገር ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው። አሁን ሁሉም ነገር ትቼ የማስበው ለተከበረው ሽማግሌ አባቴና ለተከበረችው እናቴ ነው። አንድ የምለምንህ ነገር አለኝ። ቤተሰቦቼ ምንም ነገር ቢያገኛቸው እንድትረዳልኝ አደራ እልሃለሁ”... የመቶ አለቃ ሚሴና፤ ሳ.ጉየራ. ኢን አፍሪካ ከሚለው መጽሀፍ

<u>ከአድዋ ድል ጦርነት በኋላ በአለም ዙርያ ምን አይነት ሁኔታ ተፈጠረ ?</u>

ወቅቱ የአውሮፓ ኃያላን መንግስታት አፍሪካን በቅኝ ግዛት ለመቀራመት የሚሻሙበት ወቅት ስለነበረ በምሯሯጥ ላይ የነበሩትን አገሮ ከመጠን በላይ አስደነገጣቸው። ሩጫቸውንም ለማቆም ተገደዱ። ነጭ በጥቁር ሲሸነፍ የመጀመሪያ ጊዜ በመሆኑ ሃያላንና ዘረኛ መንግስታት ተሸብረው አለቅጥ በመዋረዳቸው አፈሩ። እጃቸውንም እንዲሰበስቡ ተገደዱ። በአንጻሩም በአለም ዙርያ የሚገኙ ጥቁርና የጥቁር ህዝብ ዘርያ ያላቸው ሕዝቦች አንገታቸውን ቀና ደረታቸውን ነፋ አደረጉ፤

## <u>የዐድዋ ጦርነትና የጦር ሜዳው ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ</u>

አድዋ፤ በሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ ክልል ጫፍ ከኤርትራ አዋሳኝ ድንበር በመካከለኛው የቅርብ ርቀት ከታወቁት ከተሞች ከአክሱም፤ ከአዲግራትና ውቅሮ መካከል የሚገኝ በተራራ ሰንሰለት የታጠረ እስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ያያለው ጥንታዊ ከተማ ሲሆን ጦርነቱ የተካሄደባቸው ሥፍራዎች ትግራይና ኤርትራ በሚዋሰኑባቸው ሀ/ በአምባለጌ በኩል- በአላጌ -በአዲግራት- በእንደርታ- በአክሱም- በአጋሜ ለ/ በመቀሌ - ሐ/ በአድዋ- በአባገሪማ- ሹሉዳ ሁሉ ጣሊያን ሰራዊቱን አሰለፎ ነበር።

<u>የአድዋ ጦርነት ስያሜ</u>

ጣሊያን በመጀመሪያ በአምባለጌ ቀጥሎ በመቀሌና በተቀሩት አውደ ግንባሮች ከተሸነፈ በኋላ በመጨረሻ ያለ የሌለውን ሀይሉን በወቅቱ ቅኝ ግዛቱ ከነበረው ኤርራ በማሰባሰብ የመጨረሻ የሞትና የሽረት ትግል ቢያደርግም በማያዳግም ሁኔታ የሽንፈት ጽዋውን የጨለጠበትና የጣሊያን ባንዲራ ወርዶ የኢትዮጵያ ባንዲራ የተውለበለበበት የመጨረሻ የድል ስፍራ ሊሆን በመቻሉ የአድዋ ጦርነት እየተባለ ይጠራል።

<u>ጣሊያን ጦርነቱን</u> ለምን <u>በአድዋ በኩል ጀመረ?</u>

ጣሊያን ጦርነቱ በአድዋ በኩል የጀመረበት ምክንያት ኤርትራ በዚያ ወቅት በጣሊያን ቅኝ ግዛት ሥር ስለነበርች ለወረራና ለሎጂስቲክ (አቅርቦት) የሚመቸው ከቅኝ ግዛቱ ከኤርትራ መነሳቱን ስለሚመቸውና እንደ ምጽዋ የመሳሰሉ ወደቦች በቀላሉ ለመጠቀም ስለሚያስችለው በመሆኑ ሲሆን ወረራ ከጀመረባቸው ከኤርትራ ጀምሮ በመግፋት መላው ኢትዮጵያን ለመቆጣር እቅድ እንደነበረው ከንጉስ ኡምቤርቶ ለአፄ ምኒልክ የተላከ የማታለያ ሁለተኛ የዕርቅ ደብዳቤ ረቂቅ ያመለክታል

## የእቴጌ ጣይቱ ወደር የለሽ ብልህ ተጋድሎና የአድዋ ጦርነት

እቴጌ ጣይቱ ብልህ አዋቂና ዜዴኛ ሴት ነበሩ፤ በዚሁ ምክንያይ አጼ ምኒልክና የጦር አዛዦችን በምክር ይረዱ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ በፖለቲካ በኤኮኖሚ፤በማህበራዊና በሀይማኖታዊ ስራዎች ጥልቅ እውቀት እንደነበራቸው በሥራ አስመስክረዋል።

-- በሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም በጣሊያንና በኢትዮጵያ መንግስታት መካከል የተፈረመው የውጫሌ ውልን በቆራጥነት ለመጀመሪያ ጊዜ ያለምንም መወላወል ደፍረው በመቃወምና ሽንጣቸውን ገትረው በመከራከር ያሳዩት ቆራጥነት፤ ውሉ እንዲፈርስና ጦርነቱ አይቀሬ አድርጎታል።

-- እቴጌ ጣይቱ የውጫሌ ውልና የጣልያን ተኮል እንደደረሱበት አጼ ምኒልክ በተገኙበት ውሉ እንዲፈርስ ከጣሊያኑ ተወካይ ከኮንት አንቶሎኒ ጋር የገጠሙት ክርክር ውጤት ባለማግኘቱ ጦርነቱን ነገ አድርጉት የሚፈራ የለም ብለው ምርጫቸውን ያሳወቁ ሲሆን ይሕ የሳቸው ውሳኔ በመጨረሻም ንጉሠ ነገሥቱን በማሳመን በመንግስት ደረጃ እንዲጸድቅ አድርገዋል።

-- አፄ ምኒልክ የፈረሙትን የውጫሌ ውል ደካማ ጎን በማጤን ዳግም ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር በመስጋት ከእንገዲህ ወዲያ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚነካ፤ ሥር የሚነቅል፤ መሰረት የሚያፈርስ፤ ጉዳይ ሁሉ እኔ ሳላየው እንዳያልፈኝ በማለት ንጉሠነገስቱን አስፈቅደው አጼው በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ሁሉ በተግባር ላይ ውሎ የሚደርጉ መንግስታዊ ውሎችን ሲመለከቱ ኖረዋል።

-- የውጫሌ ውል በሥራ ላይ እንዲውል የጣሊያን መልእክተኛ ቤተመንግስት ቀርቦ የተናገረውን ሰምተው ሳለ እጃቸውና ፊታቸውን ወደሰማይ አድርገው "የዕስራኤል አምላክ ለዚህ ተእቢት ፍርድህን አውርድ መድፋቸውንና ጠመንጃቸውን ተማምነው ልባቸው ያሰበውን ይደነፋሉ ነገር ግን ሃይልና ጥንካሬ ከእግዚአብሄር ይየሚገን መሆኑን አላውቁም እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ እርዳታ ስለምናምን አንፈራቸውም" በማለት በድፍረት ተናግረዋል።

-- የውጫሌ ውል እንዲሰረዝ ኮንት አንቶሎኒን አስጠርተው ድርድር ሲደረግ በእቴጌይቱ ጠንካራ ንግግር ተበሳጭቶ ጦርንርቱ የማይቀር ነው በማለት የያዘውን ወረቀት ቀዶና ደንፍቶ ሲወጣ እቴጌ ከት ብለው በመሳቅ "ጦርነቱን ነገ አድርገው በዚህ የሚደነግጥ የለም" ብለው በታላቅ ቁጣ መልሰውለታል። ቀጥለውም እኔ ሴት ነኝ ጦርነት አልወድም፤ ሆኖም ይህን ኢትዮጵያን የጣሊያን ጥገኛ የሚያደርግ ውል ከመቀበል ጦርነት እመርጣለሁ በማለት ብቸኛ ምርጫቸውን አሳውቀዋል። በመጨረሻም የሳቸው ምርጫ ፀድቆ ጦርነቱ በተግባር ሊተረጎም ችሏል።

-- የአድዋ ጦርነት በሚመለከት አጼ ምኒልክ አንዳንድ ጊዜ የተለሳለሰ አቋም ሲያሳዩ በጦርነቱ እንዲገፉ ይገፋፉና ያደፋፍርዋቸው ነበር።



-- የአድዋ ጦርነት ላይ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙትን ሸክላ ሰሪዮች አሰባስበው የእንጀራ መጋገሪያ ምጣድና የሸክላ ድስት በማሰራት የዘመቻ ቁሳቁስ አስመርተዋል፤ ስንቅ አደራጅተዋል።

-- በአድዋ ጦርነት ዘመቻ ላይ በራሳቸው ስር የሚመራ 3ሺ እግረኛ 6ሺ ፈረሰኛ ይዘው በመዝመት በሰራዊታቸውና በደንገጡሮቻቸው ታጅበው በጦሩ መሃል ጥቁር ጃንጥላቸውን ይዘው ጥይት በላያቸው ላይ እየወረደ በሠራዊቱ መሐል በቆራጥነት እየተመላለሱ መድፍ በማስኮስና የጠላትን መሃል በመምታት ትልቅ አርአንት ያለው ስራ ሰርተዋል።

-- ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ጣምራ ሰላይ (ደብል ኤጀንት) የነበሩትን ባሻ አዋሎምና ባልደረባቸው  አቶ ገብረ እግዚአብሄርን አስጠርተው በራሥ መንገሻ ሰዩም ፊት ለሐገራቸው ኢትዮጵያ መርጃ እንዲሰሩ እንጂ ለጣሊያን ሊ አሳልፈው እንዳይሰጡ ምግብ አቅርበው " ይህ እንደሥጋ ወደሙ ቆጥራችሁ ላትክዱ ምላችሁ ብሉት" በማለት አስምለውና ቃል አስገብተው ልከዋቸዋል። በዚሁ መሠረት ሁለቱ ሰላዮች ለአድዋ ድል ወሳኝ የሆኑ እጅግ ጠቃሚ መረጃዎችን ለወገን ጦር አበርክተዋል።

-- በመቀሌ ብዙ የኢትዮጵያ ሰራዊት እልቂት ምክንያት የሆነው የጣሊያን አይደፈሬ ምሽግ በሳቸው ዘዴ ታሊያኖች የሚጠጡት ምንጭ በራሳቸው ጦር እንዲያዝ አድርገው ጦሩ እንድፈታ አድርገዋል።
-- አስራ ሁለት ሺ ሴቶችን ለዘመቻ በማዘጋጀት የውሃ ጀርካን ለሁሉም በማደል ከወንዝ ውሃ እንዲሞሉ አድርገው ተዋጊ ወታደሮች ወደሚያርፉበት ቦታ ይዘው በመኻዝ እንዲያድሉ አድርገዋል። በተጨማሪም ሌላ አንድ መቶ የሚሆኑ ሴቶችን በማደራጀት ተዋጊ ወታደሮች ቆስለው በሚመጡበት ስፍራ አስቀምጠው እንዲንከባከቡ አድርገዋል።

--ጣሊያን በአምባለጊ፤ በመቀሌና በመጨረሻም በአድዋ ጦር ግንባር በየጊዜው ባለንበት እንርጋ እስከአሁን የያዝነውን ቦታ እውቅና ከተሰጠን ጦርነቱን እናቆማለን በማለት በተለያዩ ጊዜያት ውል እያዘጋጁ ክርክር ሲደርግ ብዙዎች የተለሳለሰ አቋም ሲያሳዩ እቴጌ ጣይቱና ፊታውራሪ ኃብተጊዮርጊስ ግን ጣሊታን ጊዜ ለማግኘት ፈልጎ እንጂ እውነቱን ያለመሆኑን በመግለጽ ጠንካራ አቋም ይዘው ውድቅ እንዲሆን አድርገዋል።
-- እዲስ አበባን ቆርቁረው አዲስ አበባ የሚለው ስም አሰጥተዋል።
-- በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንግሊዞች ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ብለው ባቋቋሙት ባንክ የኢትዮጵያን ሕዝብ እዳ ውስጥ ጨምረው ሲያስቃዩት በማየታቸው ከፍተኛ ሃብት ያላቸውን ነጋዴዎችና ታላላቅ ሰዎች ገንዘብ እንዲያዋጡ አድርገው ከአፄ ምኒልክና ከራሳቸው ግምጃ ቤት ገንዘብ ጨምረው የእርሻና የንግድ ማስፋፊያ ማሕበር የሚል ባንክ አቋቋመዋል።
-- ልዩ ልዩ የቤተመንግስት አልባሳትና የቤተክርስቲያ መገናጸፊያዎችና ምንጣፎችን ከውጭ ከመግዛት ይልቅ ባለሙያ ከቱርክ በማስመጣትና ስልጠና በማመቻቸት አገር ውስጥ እንዲሰራ አድርገዋል።
-- በአገራችን ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ዘመናዊ ሆቴል ከማቋቋማቸውም በላይ ንጉሡና መኳንንቱ ገንዘብ ከፍለው እንዲመገቡ፤ኋላቀር ባሕል እንድንዲቀር አድርገዋል።
-- አፄ ምኒልክ በጠና ታመው ከሥራ በተገለሉ ከሕዳር ወር 1902 ዓ.ም ጀምሮ የመንግስቱን ሥልጣን ከአንድ ዓመት ትኩል በላይ ሲመሩ ቆይተዋል።

<u>የቴጌ ጣይቱ አጫጭር ንግግሮች....</u> "ኢትዮጵያ የጠላት እግር ረግጧት ባለቤቴ አፄ ምኒልክ በጠላት ፊት ተሰልፈው የአገሬን ሕዝብ ብዙ የግፍ እልቂት ሲጠብቀው እንደወንድ እንጂ እንደሴት በእልፍኝና በጓዳ መቆየት አይገባኝም".....ለዘማች ጦራቸው ደግሞ " ብትሞቱ ተስካራችሁን አወጣለሁ፤ ልጆቻችሁን አስተምራለሁ፤ ለቤተሰባችሁ አስፈላጊውን ሁሉ አደርጋለሁ እግዚአብሄር ከናንተ ጋር ይሁን".... ወዘተ በማለት ያበረታቱ ነበር።

ከአድዋ ጦርነት ድል በኋላ የእቴጌ ጣይቱ ፎቶግራፍ የያዘ ዜና በጀርመን፤ በፈረንሳይ፤ በሩስያ፤ በጣሊያንና በአሜሪካ ተዋጊ ንግሥት እንደ ዜኖብያ፤ ክሊዮፓትራ፤ ጆንአፍ አርክንና ታላቋ ካቴሪንን በሚል ተወዳጅነት የተላበሰ ዜና ለሁለት አመታት ሲሰራጭ ቆይቷል፡

ምንጭ አደራ መጽሃፍ በመስፍን ሀይሉ፤ አጤ ምኒልክ በጳውሎስ ኞኞ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ በተክለጻድቅ መኩርያ፤ እና The ethipian a history R.Pankhurst

<u>የእቴጌ ጣይቱ የሕይወት ታሪክ</u>
እቴጌ ጣይቱ ከእናታቸው ወ/ሮ የውዳር ከአባታቸው ከደጃዝማች ብጡል ኃ/ማርያም ነሃሴ 12 ቀን 1882 በደብረታቦር ከተማ ተወለዱ።

**ጣይቱ በአያት ቅድመ አያታቸው የአፄ ሱስንዮስ የትውልድ ሐረግ ያላቸው ሲሆን በሴት አያታቸው በኩል የኦሮሞ ዘር አላቸው።

**በተለያዩ አድባራት መንፈሳዊና የቀለም ትምህርት የተማሩ፤ ግዕዝ ቋንቋ የሚያውቁ፤ በገና መደርደር የሚችሉና ግጥም የመጻፍ ችሎታ ችሎታ የነበራቸው እመቤት ናቸው።

እቴጌ ጣይቱ ከአራቱ ቀዳሚ ባሎቻቸው አንዱ የአጼ ቴዎድሮስ የጦር አዛዥ የነበሩት ሲሆኑ ልጅ ግን እስከ መጨረሻ አልነበራቸውም።

**ጣይቱ ብጡል ሚያዝያ 25 ቀን 1875 ዓም እሁድ በአንኮበር መድሀኔዓለም ቤተክርስቲያን በአቡነ ማቴዎስ እጅ ከንጉስ ምኒልክ ጋር ጋብቻ ፈጸሙ።

** ጣይጡ ከንጉስ ምኒልክ በፊት አራት ባሎች አግብተው የፈቱ ሲሆን አንደኛው ባላቸው የአፄ ቴዎድሮስ የጦር አዛዥ ነበሩ።

**አፄ ምኒልክ ንጉሠነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ጥቅምት 24 ቀን 1882 ዓ.ም (ኖቬምበር 3 1889) ሲነግሱ ጣይቱም እቴጌ ጣይቱ ብርሀን ዘኢትዮጵያ ተብለው ጥቅምት 27 ቀን 1982 ዓ.ም ተሰየሙ።]]

# ***ክፍል 2***

## ***የየካቲት 12 ሁለት የአዲስ አበባው እልቂት፤ የሞገስ አስገዶም፤ የአብርሃ ደቦጭና የስምኦን አደፍርስ የጀግንነት ሥራ***

*ጣሊያን አገራችን ኢትዮጵያን መውረሩ ምክንያት በማድረግ አብርሃ ደቦጭ፤ ሞገስ አስገዶም፤ ስምኦን አደፍርስና ለጊዜው ስማቸው በውል የማይታወቅ ሌሎች ስድስት ጓደኞች ሆነው ሰወር ወዳለ ቦታ እየሄዱ ስለአገራቸው በጣልያን መወረርና ስለሕዝቡ ስቃይ በተለያዩ ጊዜያት እየተመካከሩ ከሰነበቱ በኋላ ሃሳባቸው ለነበጅር ወንድ ለጥ ይበሉ ገብሬና ለብላታ ወልደአማኑኤል ተናገሩ። ሹማምንቱ ግን የነሱን አቋም የሚሰልሉ እየመሰላቸው ብዙም አምነው አልተቀበሉዋቸም። እነዚህ ወጣቶች ግን ጠላትን ለማጥቃት ቆርጠው በመንሳት ዝቋላ ተራራ ድረስ በመሄድ የቦምብ አፈታት፤ አገጣጠምና አወራወር ሲያጥኑ 15 ቀን ቆይተው ተመለሱ። ከሁሉም ነገር በፊት አብርሃ ደቦጭ የካቲት አንድ ቀን 1929 ዓም ባለቤቱ ለደህንነትዋ ሲል ደቡብረ ሊባኖስገዳም ወስዶ ደብቋት ተመለሰ።*

*ዕለቱ ረቡዕ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም የጣሊያን ጦር ጠቅላይ አዛዥ የነበረው ጄኔራል ግራዚያኒ የአዲስ አበባ ከተማ ታላላቅ ሰዎችና ሕዝብ በነቂስ በታላቁ ቤተመንግስት ግቢ እንዲገኝ ጥሪ አድርጓል። በዚህ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይም የጣሊያን ታላላቅ የጦር መኮንኖች እንዲገኙ ጥብቅ ትእዛዝ ተላልፏል። በዚሁ መሰረት ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ ቦታ ቦታውን ይዞ በመጠባበቅ ላይ እያለ ግራዚያኒና የተጠሩ የጦር አለቆች በከፍተኛ ወታደራዊ ስነሥርአትና ጥብቅ ቁጥጥር በተመላበት ሁኔታ ታጅበው በቦታው ደርሰው በተዘጋጀላቸው ልዩ መድረክ ላይ ተኮለኮሉ።*

*ሁሉም ነገር ፀጥ እረጭ ሲል ግራዚያኒ ተነስቶ መነጋገሪያውን በመጨበጥ የተለመደውን የታላቂ ጣሊያን ድል አድራጊነትና ገናናነት በመደንፋት ንግግሩን ጀመረ። ቀደም ሲል በምስጢር ተደራጅተው አመቺ ቦታና ሁኔታ ሲጠባበቁ የቆዩት አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም 7 ቦንቦችን በማከታተል በግራዚያኒና በከፍተኛ የጣሊያን*

መኮንኖች ላይ በመወርወር አካባቢውን እጅግ ከፍተኛ በሆነ የፍንዳታ ድምጽ በማናወጥ ሥፍራው በሙትና በቁስለኞች እንዲጥለቀለቅ አደረጉት። ተዕቢተኛው ጄኔራል ግራዚያኒ፤ የአየር ሃይል አዛዡና በቦታው የነበሩ ታላላቅ የጣሊያን መኮንኖች በመድረኩ ዙርያ ተረፈረፉ። በዚህ ጥቃት የአየር ሀይሉ አዛዥና ሌሎች ብዙ መኮንኖች ውዲያውኑ የሞቱ ሲሆን ግራዚያኒ ትልቅ ጉዳት ደርሶበት ከረጅም ሕክምና በኋላ ሊድን ችሏል።

ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች በንብ ጥለው አደጋ ካደረሱ በኋላ በቤተመንግስቱ የኋላ በር በማምለጥ ተዘጋጅቶ ይጠብቃቸው የነበረው ስምኦን አደፍርስ የተባለው ተባባሪያቸው በግል መኪናው አሳፍሮ ፍቼ ድረስ በመውሰድ ከነራስ አበበና ከራስ መስፍን ስለሺ ጦር ጋር እንዲገናኙ አደርጎ ወደአዲስ አበባ ሊመለስ ችሏል።


ስምኦን አደፍርስ ሁለቱ ጀግኖች አድርሶ አዲስ አበባ ተመልሶ ጥቂት ቀናት ከሰነበተ በኋላ በሳምንቱ በጥቆማ ተይዞ ታሰረና እጅግ አስቃቂ ምርመራዎችን ተደርጎበት ምስጢር ሊያወጣ ባለመቻሉ ሚያዝያ 29 ቀን 1929 ዓም በ24 ዓመቱ ጣልያኖች በጭካኔ ገድለውታል።

ጣሊያን እነዚህ ጀግና ኢትዮጵያውያንን ሞገስ አስገዶምና አብርሃ ደቦጭ ጠቁሞ ላስያዘ ሰው 10 ሺ ጥሬ ብር (ጠገራ ብር ) ወሮታ የሚከፍል መሆኑን ማስታውቂያ በማውጣቱ አደገኛ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ተገንዝበው ከአገር ለመውጣትና በሱዳን በኩል ለመሰደድ በጉዞ ላይ እያሉ መተማ አካባቢ በስህተት የርስ በርስ ግጭት ውስጥ ገብተው በ1932 ዓም በጥይት ተመተውሞተዋል።

በሞገስ አስገዶም፥በአብርሃ ደቦጭና፥ በስምኦን አደፍርስ ቅንጅታዊ አሰራር በግራዚያኒና በተከታዮቹ ላይ በደረሰው ውጤታማ ጥቃት ምክንያት።
1ኛ/አስካሪ የተባሉ የጣሊያን ቅጥረኛ ባንዳዎች የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ላይ ወደር የሌለው ጭፍጨፋ በማደረግ ሰላሳ ሺህ ህዝብ ጨርሰዋል።
2ኛ/የከተማው ነዋሪ እቤቱ ውስጥ እንዳለ ከነህይወቱ በሳት እንዲጋይ አድርገዋል፥፤
3ኛ/የአዲስ አበባና አካባቢዋ ወንዞች በሙታን ደም ቀልተው ሰንበተዋል
4/ኛ/ከዚህ የጅምላ እልቂት የተረፉትን ተለቅመው እየታሰሩ ወደግዞት ተወርውረዋል።ከነዚህ ስመጥሩኢትዮጵያውያን መካከል እነ ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ይገኙባቸዋል።


1./ሞገስ አስገዶም


2/.አብርሃ ደቦጭ


3/.ስምኦን አደፍርስ

የሕይወት ታሪካቸው  አብርሃ ደቦጭ_በ1900 ኤርትራ ውስጥ በሠራዬ አውራጃ ተወልዶ  እስከ ጠላት ወረራ ድረስ አዲስ አበባ በመጀመርያ ዘመናዊ ትምህርት ከተከታተለ በኋላ በመምህርነት ሙያ ተቀጥሮ አገሩን አገልግሏል ። በጠላት ወረራውም ጊዜ ከደጃዝማች ፍቅረማርያም አባተጫን ጋር በመነጋገር የመረጃ ሥራ እያከናወነ ቆይቷል።

ሞገሥ አስገዶም በ1898 ኤርትራ ውስጥ አካለ ጉዛይ አውራጃ ተወልዶ አዲስ አበባ በመምጣት ዘመናዊ ትምህርቱን ካጥናቀቀ በኋላ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የመሬት ምዝገባ ቢሮ ሰራትኛ በመሆን  እያገለገል እስከጠላት ወረራ ድረስ ቆይቷል።

ስምኦን አደፍርስ ከአባቱ አቶ አደፍርስ አድጎ እና ከእናቱ ክወይዘሮ ወለተብርሃን መሸሻ በ1905 ዓ ም ጎባ ውስጥ ተወልዶ የመጀመርያውን ትምህርት በዚያው አካባቢ ካጠንቀቀ በኋላ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ዘመናዊ ትምህርትቱን ጨርሶ የግል ንግድ በማቋቋም የታክሲ ሥራ ሲያከናውን ቆይቶ ነበር።

1 

2 

3 


1/ የካቲት 12 መታሰቢያ ሃውልት

2/ ቢንቶ ሞስሎኒ

3/ገራዚያኒ

ምስጋና የተለያዩ የኮምፒተር ቴክኒክ ችግር የሚያቃልሉልኝ
አቶ ይልማ ዘርይሁንን በራሴና በዜግነት መጽሔት ስም
ከልብ አመሰናቸዋለሁ

**ኢትዮጵያ ከልጆችዋ ጋር በሰላምና በነፃነት ተከብራ ትኑር !!!!**

[ዋና አዘጋጅ ይርጋዓለም ኀበዜ {አገሬ ኢትዮጵያ} 214 293 2547]

ቤት ለመግዛትና ለመሸጥ
ሲፈልጉ   ወ/ሮ ሕይወት ምላኩ











